የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ መጋቢት ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 27
ADDIS ABABA, 10th April 2017

**<u>ማውጫ</u>**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፬/፪ሺ፱ ዓ.ም

የመንግሥት ዕዳ ሰነድ አዋጅ……………………ገፅ ፱ሺ፭፻፸፮

**CONTENT**

PROCLAMATION NO. 994/2017

Government Bond Proclamation………………page 9576

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፬/፪ሺ፱

## ስለ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች (ቦንዶች) የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ካፒታል ለማሣደግ የሚውለው ገንዘብ በመንግሥት ዕዳ ሰነድ (ቦንድ) እንዲከፈል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የመንግሥት ዕዳ ሰነድ አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፬/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር:-

## PROCLAMATION NO. 994/2017

## PROCLAMATION ON GOVERNMENT BOND

**Whereas** it has become necessary to issue Government bond to be used for raising the capital of the Commercial Bank of Ethiopia,

**Now,therefore** ,in accordance with Article 55(1) of the Constitution ,it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### General

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as the" Government Bond Proclamation No. 994/2017"

**2. Power of Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩/ብር ፳፮ ቢሊዮን ፭፻ ሚሊዮን (ሃያ ስድስት ቢሊዮን አምስት መቶ ሚሊዮን ብር) ዋጋ ያለው የመንግሥት ዕዳ ሰነድ እንዲያወጣ፤

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን የመንግሥት ዕዳ ሰነድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ካፒታል ለማሣደግ እንዲያውል በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

1/ to issue Government Bond of Birr 26,500,000,00 (twenty six billion five thousand million birr).

2/ utilize the Government Bond issued in accordance with this Proclamation to raise the capital of the Commercial Bank of Ethiopia.

## ክፍል ሁለት

## ስለክፍያና ወለድ

### ፫. ክፍያ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚወጡት የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች ከአምስት ዓመታት የችሮታ ጊዜ በኋላ በ ፲ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ተከፍለው ይጠናቀቃሉ።

### ፬. ወለድ

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡት የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች ወለድ አይከፈልባቸውም።

## ክፍል ሦስት

## ልዩልዩ ድንጋጌዎች

### ፭. ከቀረጥ ግብር ነፃ መሆን

ከመንግሥት ዕዳ ቦንዶች ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ወይም ሰነዶች ላይ የቴምብር ቀረጥ ወይም ሌላ ማናቸውም ቀረጥና ግብር አይከፈልም።

## PART TWO

## REDEMPTION AND INTEREST

### 3. Redemption

Government Bond issued in accordance with Article 2 above shall be redeemed in 10 years period after a grace period of five years.

### 4. Interest

Government Bond issued in accordance with this Proclamation shall bear no interest.

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 5. Exemption From Taxes

No Stamp duty or any other tax shall be levied on any transaction or document relating to the Government Bonds.

፮. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**6. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**አዲስ አበባ መጋቢት ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**Done at Addis Ababa, this 10th day of April,2017**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**